# የባንዳ ባንዳዎች

ከንጉሤ ጋማ

ጠላትማ ምንጊዜም ጠላት ነዉ
አስቀድሞ መግደል አሾክሿኪዉን ነዉ፣
የሚለዉ ስንኝ ያለምክንያት አልተቋጠረም፡፡
ማንነቱን በሚገባ ለይተዉ ከተረዱት ጠላት ይበልጥ ትልቁን ጉዳት ሊያደርስና ሊያስጠ ቃ የሚችለዉ ለተለያየ ጥቅም ሲል ከጠላት ጋር በእጅ አዙር በመመሳጠር የቆመ አካል እንደሆነ ለማስገንዘብ ነዉ፡፡

የኢጣሊያን መንግስት አገራችንን በወረረበት ወቅት የንፁኃን ዜጎቻችንና የጦር መሪዎች ደም በግፍ እንዲፈስ ያደረጉ፣ ለጠላት ጦር መዉጫ መግቢያዉን እየጠቆሙ ነፃነታችን እንዲረገጥ፣ የግዛት አንድነታችን እንዲደፈር ያስደረጉት ለጊዜያዊ ጥቅም ተገዝተዉ ከወራሪዉ መንግስት ጋር በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ መንገድ የተሰለፉ ኢትዮጵያዊያን እንደሆኑ አንዘነጋዉም፡፡

ባንዳ ተብለዉ የሚጠሩት እነዚህ የዉስጥ ጠላቶች ከሚገባዉ በላይ ለስልጣንና ለጥቅም ከሚመነጭ ፍላጎት በመነሳት «የእኔ» የሚሉትን አገርና ሕዝብ ለባዕድ አሳልፈዉ የሚሰጡ ከሃዲዎች ናቸዉ፡፡ ባንዳነት ከቤተሰባዊ አስተዳደግ ወይንም ከአካባቢያዊ አመለካከት የሚፈጠር ከፍተኛ ደረጃ ላይ የደረሰ የስብዕና ድክመት እንደሆነ የስነ አዕምሮ ጠበብት ይገልፃሉ፡፡ በግልፅ የማይታይ የአዕምሮ መዛባት በሽታ ተጠቂዎች የዉስጣዊ ፍላጎታቸዉ ግጭት የሚገለፅበት ዓይነተኛ መለያ እንደሆነም ይነገራል፡፡ መለስ ዜናዊ፣ ስብሃት ነጋ፣ ስዩም መስፍንና ሌሎችም ከደደቢት ጫካ ተማምለዉ፣ ብዙዎችን መስዋዕት በማድረግ በንፁሃን ደም ተረማምደዉ እዚህ የደረሱት ባንዳዎች ከላይ በተገለፀዉ እዉነታ መሰረት የኢትዮጵያን ታላቅነት፣ ሰላምና ዕድገት ማየት የማይፈልጉ ኃይሎች በትግራይ ሕዝብ ነፃ አዉጪ ስም፣ አደራጅተዉና አስታጥቀዉ ኢትዮጵያ የምትባለዉን ታሪካዊ አገር ለማፈራረስ ያሰማሯቸዉ እንደሆነ አንዘነጋዉም፡፡

***ሥልጣን ተሻሚ ትግሬዎችና የኢትዮጵያ አንድነት*** በሚል መፅሃፋቸዉ ተክሌ የሻዉ፣ «ለትግራይ ሕዝብ ፍላጎት ሳይሆን የእራሳቸዉን ጥቅም በሰፊዉ ሕዝብ ላይ ለማረጋገጥ በሚደርሱበት የግል ዉሳኔ ምክንያት ከጥንት ጀምሮ ሥልጣን ተሻሚ ትግሬዎች ወደ ፖለቲካ መድረክ ብቅ ባሉ ቁጥር ለፍላጎታቸዉ መሳካት፣ ማስፈፀሚያ መሳሪያ የሚያደርጉት የአገሪቱን አንዱን ክፍል /ቀይ ባህርን/ ለባዕድ አሳልፎ መስጠትና ለዉጭ ኃይሎች ፍላጎት ተገዢና ተንበርካኪ መሆንን ነዉ» በማለት ጠቅሰዋል፡፡ በዚሁ መፅሐፋቸዉ፣ «ወያኔን ካለፉት የሚለየዉ ዘርን /ጎሳን/ መሰረት ባደረገ የፖለቲካ ቡድንና ሽርክና በተደራጀ መልክ ከኢትዮጵያ የሩቅና የቅርብ፣ ነባርና ጊዜያዊ ጠላቶች ጋር በማበር የኢትዮጵያን ተፈጥሯዊ፣ ታሪካዊና ባህላዊ የሆነዉን ቀይ ባህርን፣ የኢትዮጵያዊነት መነሻ መሰረት የሆነችዉን ባህረ ነጋሽን ወይም መረብ ምላሽን ለጠ ባብና ጊዜያዊ ፍላጎታቸዉ ሲሉ ማስገንጠላቸዉና የቀይ ባህርን የኢትዮጵያ በርነት መካዳቸዉ ነዉ» በማለት ገልፀዉታል፡፡

የወያኔን አፍራሽ ተልዕኮ በርካታ አገር ወዳድ ምሁራን እንዲሁም በድርጅቱ ዉስጥ በአመራር አባልነት ደረጃ የነበሩ ግለሰቦች ሳይቀሩ በመደጋገም ሲገልፁት የነበረ ሀቅ ነዉ፡፡ ከነዚህም መካከል ተስፋይ አፅበሃ፣ ካህሳይ በርሄ፣ ዶ/ር አረጋዊ በርሄ፣ ገብረ

መድህን አርአያ፣ /ጌታቸዉ ጀቤሳ/ ያሬድ ጥበቡ፣ ፕ/ር ተኮላ ሃጎስ፣ ፕ/ር ንጉሴ አየለ እና ሌሎችም ይጠቀሳሉ።

ይህ ብሂርተኛ ቡድን ከአነሳሱ እ/ኤ/አ በ1919 ብሔራዊ የጀርመን ሶሻሊስት ሠራተኛ ፓርቲ በሚል ስም ከተቋቋመዉ የአዶልፍ ሂትለር የፈላጭ ቆራጭ አምባገነናዊ ድርጅት የሚጋራቸዉ የናዚ ባህሪያት አሉት።

1/ የ«አርያን» ዘር / የጀርመን ሕዝብ/ በምስራቅና በመካከለኛዉ አዉሮፓ ካለዉ ዘር የ«በላይ» እንደሆነ የሚያምን እንደሆነ ሁሉ የመለስ/ስብሃት ቡድንም እራሱን ከ«ወርቅ» የሚያነፃፅር ዘር ያለዉ አድርጎ የሚቆጥር ነዉ። ይህ ደግሞ ለሌላዉ የኢትዮጵያ ሕዝብ ያለዉን ንቀት በተለይም «እንደመንግስት ቆሜያለሁ» ከሚል ኃይል የማይጠበቅ ስነ ምግባር እንደሆን አሌ አይባልም።

2/ በወታደራዊ ኃይል በመታገዝ፣ ግዛት በማስፋፋትና ጠንካራ ኢኮኖሚያዊ መሰረት ያለዉ የጀርመን መንግስትን በሌሎች መንግስታት ኪሳራ በአዉሮፓ መገንባት፣ ከዚህ ጋር የጀርመን ሕዝብ ጠላት ናቸዉ ብሎ ያመነባቸዉን ነገደ እስራኤል በተለያየ ዘዴ ከአዉሮፓ ምድር ማጥፋት ሌላይኛዉ የናዚ እምነት ነበር። ይህ የሂትለር እምነት ለሁለተኛዉ የዓለም ጦርነት መቀስቀስና ዓመታት ላስቆጠረ የሕዝብ ዕልቂትና ዉድመት ምክንያት እንደሆነ እንረዳለን። በተመሳሳይ መልኩ ከሌሎች የወያኔ አባላት እዉቅና ዉጭ የመለስ/ስብሃት ቡድን በ1976 የትግራይ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክን ለመመስረት የሚያስችል ማኒፌስቶ በሚስጥር በማርቀቅ፣ ይህንኑ ፀረ ኢትዮጵያ የሆነ አፍራሽ አቋም የሚቃወሙ ኃይሎችን አረመኔያዊ በሆነ ስልት በማስወገድ እዚህ ደርሰዋል። የኢትዮጵያን አንድነት የደገፉ፣ የኤርትራን ነፃነት የተቃወሙ ዜጎች ዕጣ ፈንታ፣ ግድያ፣ እስራት፣ ስደትና እንግልት እንደሆነ ገሃድ ነዉ።
ሀብረ ብሔራዊ ተዋፅዖ የነበረዉን የአገሪቱን የመከላከያ ኃይል በትኖ በምትኩ ከአንድ ብሄር በተዉጣጣ ሠራዊት ማደራጀት፣....... በአፍሪቃ በዉጊያ ብቃቱ ምስጉን ከሆኑት አንዱ የሆነዉን የአየር ኃይል ተቋም የአገሪቱን ሁለንተናዊ ግዛት ለመቆጣጠር በሚያስችል ረገድ በአማካይ ዕቅድ ከተደራጀበት ስፍራ ወደ ትግራይ የተዛወረበት ምክንያት፣ ........ከአፋር፣ከወሎና ከጎንደር የተወሰኑ አካባቢዎች ተቆርጠዉ የትግራይን ግዛት ለማስፋፋት የተወሰደዉ እርምጃ፣......በምንም መመዘኛ ከሌሎች ክልሎች ባልተመጣጠነ መንገድ ትግራይን በኢንዱስትሪ የበለፀገች፣ በመሠረተ ልማት ተቋሞች ያደገች፣ በየመስኩ የሠለጠነ የሰዉ ኃይል ባለቤት የሆነችና በጠቅላላዉ ጠንካራ የኢኮኖሚ መሠረት እንዲኖራት ለማድረግ እስከ ዛሬ የሚደረገዉ መረባረብ ለምን እንደሆነ ለመገመት ፈላስፋ መሆንን አይጠይቅም።
ሕዝቧ የረሃብ ተምሳሌት የሆነባትን አገር ደቃ ገበሬ በማፈናቀል ለም መሬቶቿን እጅግ ባልተመጣጠነ ዋጋ ለባዕዳን በኢንቬስትሜንት ስም በዓመታት ለሚቆጠር ጊዜ መቸብቸብ፣....... ዓለም አቀፋዊ ሕጋዊ የድንበር ማካለል ደንብን ባልተከተለ መንገድ ከጎንደር እስከ ጋምቤላ ጠረፍ ከሰሜን እስከ ደቡብ ከ1600 ኪሎ ሜትር በላይ የአገሪቱን ግዛት ገምሶ ለሱዳን መንግስት በችሮታ መለገስ .......በሂደት ኢትዮጵያ የምትባል ጠንካራ አገር እንዳትኖር ለማድረግ እንደሆነ ለማንም ግልፅ ነዉ።

እነዚህ ሁሉ ቅድመ ሁኔታዎች የመለስ/ስብሃት ቡድን ከሌሎች የወያኔ አባላት እዉቅና ዉጭ በሚስጥር ያረቀቁትን የትግራይ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክን ምስረታ ማኒፌስቶ አመቺ ጊዜ ሲፈቅድ በ«ህገ መንግስት» ተብዬዉ ሰነድ አንቀፅ 39 መሰረት በኢትዮጵያዊነቱ የሚያምነዉ የትግራይ ሕዝብ ተቀበለ/አልተቀበለ በጠብመጃ ኃይልም

ሆነ በተለመደ የሽፍጥ ዘዴ ተፈፃሚ ለማድረግ እንደሆነ ብዙዎች በርግጠኛነት ይረዱታል።

ይህ አፍራሽ ተግባር ደግሞ ተፈፃሚ መሆን ያለበት አሁን ያለዉ የወያኔ መንግስት በስልጣን ላይ እስካለ ብቻ እንደሆነ፣ «እኛ ከሥልጣን ከተወገድን ኢትዮጵያ የምትባል አገር አትኖርም፣ በሩዋንዳ የታየዉ ዓይነት የዘር ዕልቂት ይደርሳል»በማለት ዘወትር የሚያሰሙት ማስፈራራት ከዚሁ ኢትዮጵያን ከማፈራረስ ዕቅዳቸዉ ጋር የተያያዘ የዕብሪት አነጋገር እንደሆነ ግልፅ ነዉ።

የመለስና የቢጤዎቹ ባንዳነትና ጠላትነት ምንም የማያጠራጥር በመሆኑ የሚፈፅሙት የክህደት ወንጀል ከስብዕናቸዉ አስነዋሪ ድክመት የመነጨ ነዉና ማንነታቸዉ ላያጠያይቅ ይችላል።

እነዚህ የለየላቸዉ ቀንደኛ ጠላቶቻችን የሚፈፅሙትን ወንጀል ለማገዝ ከጎናቸዉ የተሰለፉትን የባንዳ ባንዳዎች ማንነትና ተልዕኮ ግን እጅግ የሚያጠያይቅ ነዉ።

እነዚህንም በተለያየ ደረጃ ለይተን መመልከት ይገባናል።

## 1/ ወያኔን በጭፍን የሚደግፉ የትግራይ ተወላጆች

አብዛኞዎቹ በትግራይ ተወላጅነታቸዉ ብቻ ድርጅቱ የሚያራምደዉ እኩይ ተግባር ነገ ሊያስከትል የሚችለዉ ቀዉስ በትክክል ሳይገባቸዉ ቀርቶ ሳይሆን አዉቀዉ ያላወቁ በመምሰል በጭፍን ወያኔን የሚደግፉ ናቸዉ፣ ቁጥራቸዉም ቀላል አይደለም። «ለነገዉ ይታሰብበታል» በሚል ግምት የጥቅም ተካፋይ የሆኑት ለጥቅማቸዉ ሲሉ፣ ጥቅም የማያገኙት ደግሞ በራሳቸዉ የማይተማመኑ ደካሞች የወያኔ በስልጣን ላይ መኖር የእነሱ መኖር፣ የወያኔ ዉድቀት ዉድቀታቸዉ አድርገዉ በመቁጠር ሁሉንም እያዩ በዝምታ ማለፍን የመረጡ ናቸዉ። ከአገርና ከወገን ዓላማ ይልቅ የድርጅትና የጎሳ ወገንተኝነት ዓይናቸዉን ያወራቸዉ የፓርቲዉ አባላትና ካድሬዎች በዚህ ምድብ ዉስጥ ይገኛሉ። ከዚህ በተረፈ በአገሪቱ የሚታየዉ የፖለቲካ ቀዉስ ምኑም ሳይገባቸዉ እንደገደል ማሚቶ የሚሏቸዉን እያስተጋቡ በጀሌነት ከአምባገነኑ ስርዓት ጋር የተሰለፉ ቁጥራቸዉ ጥቂት አይደለም። እዚህ ላይ በትግራይ ተወላጅነታቸዉ ምክንያት ብቻ «የወያኔ ደጋፊ ተደርገን ስለምንቆጠር የገለልተኝነት አቋም ብንይዝም በሌሎች ክልል ተወላጆች ዘንድ ተቀባይነት አይኖረንም» በሚል ምክንያት ለወያኔ ያደሩም እንዳሉ መዘንጋት የለብንም።

## 2/ የወያኔን ዓላማ በጭፍን የሚያራምዱ የሌሎች ክልሎች ተወላጆች

በአገርና በወገን ላይ ትልቁን በደል እየፈፀሙ ያሉት በዚህ ምድብ ዉስጥ የተካተቱት የቀን ጅቦች ናቸዉ።

### 2.1 የወያኔ ምርኮኛ ሆነዉ ከመነሻዉ አብረዉ የመጡ ሆዳሞች፣

እነዚህ ከመለስ/ስብሃት በደረጃ ተዋረድ የቆሙ ከፍተኛ የአገርና የወገን ጠ ላቶች ናቸዉ። እነመለስ ክልላቸዉን፣ሕዝባቸዉንና እራሳቸዉን በኢትዮጵያ ኪሳራ በመጥቀም ላይ ሲገኙ እነዚህ «እንወክለዋለን» በማለት በስሙ የተደራጁበት ሕዝብ መብቱ ሲረገጥ፣ ያለ ህግ ሲገደልና ሲታሰር ከወያኔ ጎን በመቆም የሚረግጡት፣ የሚገድሉትና የሚያስሩት ናቸዉ። ሕዝቡ የልማት ተጠቃሚ ሳይሆን የተገላቢጦሽ ከርስቱ ሲፈናቀል፣ ግዛቱ እየተቆረሰ ከሌላ ሲካለል፣ ለባዕዳን ሲሰጥ አብረዉ አስፈፃሚ

አካል ሆነዉ የሚያገለግሉ ከግል ሆድና ንብረታቸዉ ባሻገር ምንም የማይፈይዱ መገልገያዎች ናቸዉ።
መቼም ምርኮኛ መብት የለዉምና ወያኔ ለመንግስት ስልጣን ከመብቃቱ በፊት ጫካ እያሉ በተለያየ መንገድ ያሰቃያቸዉ፣እጃቸዉን ጠምዝዞ፣አፍንጫቸዉን ሰንጎ ሬት ሬት የሚል ፕሮግራሙን እንዲጨልጡ አድርጓቸዉ ሊሆን ይችላል። ይሁን እንጂ አብረዉ ሲከርሙ በየዕለቱ የወያኔ ተግባር የጫካ ሕልሙን «እንወክለዋለን» ብለዉ በሚገምቱት ወገናቸዉና ክልላቸዉ ኪሳራ እዉን ለማድረግ ሲፍጨረጨር «አሻፈረኝ» የሚል ወኔ ባይፈጥርባቸዉ እንኳ አብረዉ ከማሽቃበጥና ከማስፈፀም መቆጠብ ነበረባቸዉ።

እራሳቸዉ ነፃ ሳይሆኑ ክልላቸዉንና ሕዝባቸዉን «ነፃ» ለማዉጣት መነሳታቸዉን በሙሉ አፍ መግለፅ እንዴት አያሳፍራቸዉም? የቀድሞዉ ኢህዴን የአሁኑ ብአዴን፣ የኦህዴድ፣ የኢትዮጵያ ዲሞክራሲያዊ መኮንኖች አብዮታዊ ንቅናቄና ሌሎችም የምርኮኛ ስብስቦች በዚህ ዉስጥ ይካተታሉ። በፖለቲካ ትግል ዉስጥ ጊዜ፣ቦታና አጋጣሚ የሚፈቅዱት ምቹ ሁኔታ እስኪፈጠር ድረስ የልብን በልብ ይዞ አሸምቆ መጠበቅ ያለ ነዉ። በጥቂቱ ከሃያ ላላነሰ ዓመት ስብዕናቸዉ እየተረገጠ ለዚህ አምባገነን ስርዓት ማጎብደዳቸዉ ምንም አይሰማቸዉም፣ ወይንስ «ቆምኩለት» የሚሉትን ዓላማ ትተዉ እራሳቸዉን እንኳ ነፃ ለማድረግ ምቹ ሁኔታ አላገኙም? እጅግ አጠያያቂ ነዉ።
እነዚህ ሆዳሞች በታዘብኳቸዉ መጠን ከረዥም ዓመታት በፊት የሰማሁትን የአንድ የጅብ መንጋ ታሪክ ያስታዉሱኛል፣ይመሳሰሉብኛልም። በደቡብ ኢትዮጵያ ዉስጥ የሚገኝ አንድ ለየት ያለ የጅብ ዘር ነዉ። ከሞተ ቀናት ያስቆጠረ የበከተ ከብት አሽትተዉ ጅቦቹ ከያቅጣጫዉ ተጯጩኸዉ ጊዜዉ ለዓይን ያዝ ሲደርግ ከሞተዉ ከብት በቅርብ ርቀት ይሰበሰቡና አድፍጠዉ ይጠብቃሉ። ከሰዓታት ቆይታ በኋላ ከመካከላቸዉ በዕድሜ የገፋዉ አንጋፋ ጅብ ተነስቶ ከተጋደመዉ ከብት አንድ ክፍሉን እንደገነጠለ ሁሉም ካደፈጡበት ባለ ጉልበታቸዉ ተጠቅመዉ የየድርሻቸዉን በመገነጣጠ ል በጥቂት ደቂቃዎች ልዩነት በያቅጣጫዉ ይነጉዳሉ። እናም የመለስ/ስብሃት ቡድን በስልጣን መቆየት አልሳካለት ብሎ በቁም ከገደላት አገራችን ላይ የድርሻዉን ይዞ ወደራሱ ሪፑብሊክ ሲያቀና እነሱም የየድርሻቸዉን ገንጥለዉ በያቅጣጫዉ ለመንጎድ አድፍጠዉ የሚጠብቁ ያ የጅብ መንጋ ይመስሉኛል። ይህ ዓይነት ዝርያ እስከሌላቸዉ ድረስ ይህ ሁሉ አገር የመግደል እርምጃ በትዕቢት ሲፈፀም ምን ይጠብቃሉ?

የክልላቸዉ ታሪካዊ መሬት ከወሎና ከጎንደር ተቆርሶ ወደ ትግራይ ሲዋሰን፣ ይባስ ብሎ በዚህ ዮሃንስ የተሰዉበት በዚያ ቴዎድሮስ በጀግንነት የወደቁበት መተማና ቋራ ያለሕዝብ ይሁንታ እና ዕወቅና ለሱዳን መንግስት ገፀ በረከት ሲሰጥ እነአዲሱ ለገሠ፣ተፈራ ዋልዋ፣ አያሌዉ ጎበዜ እና ሌሎችም «የክልሉ ጉዳይ ጉዳያችን» ያሉ ሰዎች ቃል ያለመተንፈሳቸዉ ከምን የመጣ ነዉ?

እራሱን በራሱ የመምራት አኩሪ የሆነ የገዳ ባህላዊ የአስተዳደር ስልት ያለዉ፣ አገሪቱ ካላት አጠቃላይ የተፈጥሮ ሀብት የአብዛኛዉ ባለቤት የሆነዉ፣ በያዘዉ የቆዳ ስፋትና የሕዝብ ብዛት የአንበሳዉ ድርሻ የሚገባዉ የኦሮሚያ ክልል ሕዝብ የመሰረተ ልማት ተጠቃሚና ተመጣጣኝ የኢንዱስትሪ ተቋማት ሳይኖሩት ትግራይን በምጣኔ ሀብት ለማፈርጠም የአገሪቱን የዉጭ ምንዛሪ በማሟጠጥ የሚደረገዉ ዓይን ያወጣ አሳፋሪ ተግባር ሲፈፀም፣ እነኩማ ደመቅሳ/ታዬ ተክለማርያም/፣ አባዱላ ገመዳ/ምናሴ ወልደ ጊዮርጊስ/፣ሙክታር ከድር የመሳሰሉት ላይረዱት ቢችሉ እንኳ ግርማ ብሩ ከምጣኔ ሀብት ሙያና ዕዉቀታቸዉ አኳያ እንዴት በዝምታ ሊያልፉት ያስችላቸዋል?

የወያኔ መንግስት በክልል መስተዳደሩ ዉስጥ ያለዉ ጣልቃገብነት በፈጠረዉ ያለመግባባት ምክንያት በቅደም ተከተል ወህኒ ቤት ተጥለዉ ያለህግ በእስር እንዲማቅቁ የተደረጉት የጋምቤላ ፕሬዝዳንቶች ኦኬሎ ኦማንና ኦኬሎ ኝጌሎ፣ ዕዉቁ የሰብዓዊ መብት ተሟጋችና የአዲሲቱ ኢትዮጵያ የወዳጅነት ንቅናቄ /Solidarity Movement of New Ethiopia/ SMNE/ መስራች ኦባንግ ሜቶ፣ ኒክዎ ኦቻላ እና ሌሎችም በኢትዮጵያዊነታቸዉና በአኝዋክነታቸዉ የሚመኩ ዜጎች የበቀሉባት ጋምቤላ የሰዉ ድኃ ሆና እንደ ዶ/ር ባርናባስ ባሉ የወያኔ ካድሬዎች ትዕዛዝ በገዛ ወገኖቹ ላይ የዘር ማጥፋት ወንጀል የፈፀመና ያስፈፀመዉ ኡመድ ኡባንግ ዛሬ በክልል ፕሬዝዳንትነት ተሹሞ የክልሉን መሬት ለሱዳን መንግስት በስጦታ፣ ለሕንድና ለሼህ አላሙዲን ኩባንያዎች በኢንቬስትሜንት ስም እየሸነሸነ ሲሰጥ ምን ያህል ወንጀል በመፈፀም ላይ እንዳለ አይገባዉም?

ከለገደንቢ በሚመረተዉ ወርቅ ጊዜ የሰጣቸዉ የወያኔ መሪዎች የክልል ልማታቸዉን ሲያካሂዱ፣ ከሚድሮክ የተሻረኩት ባለስልጣናት ደግሞ የየድርሻቸዉን በዉጭ ባንኮች ሲቀራመቱ፣ «ባካባቢያችን መንገድ፣ የንፁህ የመጠጥ ዉኃ ፕሮጀክት የመሳሰሉ የመሠረተ ልማት አዉታሮች ይዘርጉልን» ብሎ ሕጋዊ ጥያቄ ያቀረበዉ የአካባቢዉ ነዋሪ በመንግስት የፀጥታ ኃይሎች ሲገደል፣ ሲታሰርና ሲንገላታ በአካባቢዉ ሕዝብ ስም የስልጣን ኮርቻ ላይ ተፈናጠዉ ድርጊቱን የሚያስፈፅሙት ሺፈራዉ ሽጉጤ፣ ኃይለማርያም ደሳለኝ እና የመሳሰሉት አካላት ከቶ ምን ይሰማቸዉ ይሆን?

በአምባገነኑ የወያኔ መንግስት የፀጥታ ኃይሎች አማካይነት በኦጋዴን ሕዝብ ላይ እጅግ ዘግናኝ የዘር ማጥፋት ወንጀል በሚፈፀምበት ወቅት የተባበሩት መንግስታት የሰብዓዊ መብት ጥበቃ ድርጅት /UN Human Rights Watch/ ድርጊቱን በማዉገዝ በዓለም አቀፍ ደረጃ እንዲጣራ ሲጠይቅ፣ ሌሎችም የሰብዓዊ ድርጅቶች መለስ ዜናዊ በሄግ የዓለም አቀፍ ፍርድ ቤት በወንጀል መጠየቅ ይኖርበታል በማለት ሲወተዉቱ እነ ዳዉድ መሃመድ ዓሊ ምን ይሰማቸዉ ይሆን?
የእኔ በሚሉት አካባቢና ወገን ላይ የከፋ ጥቃት ሲፈፀም አይቶ በዝምታ የሚያልፍ ምን ዓይነት ህሊና ሊሆን እንደሚችል ግራ ያጋባል።
አሜሪካዊዉ ሳይንቲስት ሮበርት አንድሬይ **/Territorial Imperative/** በሚል የፅንሰ ሃሳብ ስራዉ ......ሰዎችና እንስሳት «የእኔ ነዉ» ብለዉ በሚገምቱት አካባቢያዊ ክልል ወይንም ድንበር ዉስጥ ያላቸዉን ባለቤትነት ለማስጠበቅ ተመሳሳይ ባህሪይ እንዳላቸዉ ይናገራል። በዚህ ምድብ ዉስጥ የሚገኙት የወያኔ ምርኮኞች በዚህ ፅንሰ ሃሳብ ዉስጥ የማይገቡ ከእንስሳትም ያነሱ ሆነዉ መታየታቸዉ አገራችን በምን ዓይነት ሰዎች በመመራት ላይ እንደምትገኝ ብዙ የሚያነጋግር ነዉ።

## 2.2 ወያኔ ወደ ስልጣን ከመጣ በኋላ ጠፍጥፎ የሰራቸዉ «ነፃ አዉጪ» ተብዬዎችና ከጫካ የመጣዉን የምርኮኞች ስብስብ የተቀላቀሉ ወዶ ገቦች፣

በዚህ ምድብ ዉስጥ የምናገኛቸዉ ከላይ በተራ ቁጥር 2.1 ከተጠቀሱት ለየት የሚያደርጋቸዉ በትግል ሜዳ ቃታ ስበዉ ተሸንፈዉ እጃቸዉን የሰጡ ሳይሆን የዘር ፖለቲካ ስቧቸዉ፣የማንነታቸዉን ህረግ በመምዘዝ «ለሌላዉ የዘነበዉ ቢያካፋልን» በማለት እራሳቸዉን አሳልፈዉ የሰጡ ወዶ ገቦች ናቸዉ። በርግጥ «ተገድጄ ቅፅ እንድሞላ ተደርጌ ነዉ» ሊሉ የሚችሉ እንዳሉ ይታወቃል። ከጫካ ከመጣዉ ቡድን አብዛኞዎቹ በትምህርትም ሆነ በሙያ በተሻለ ደረጃ የሚገኙ እንደሆኑም እንረዳለን። አብዛኞዎቹ የክልል ስራ አስፈፃሚ አካላት፣ በመንግስት መስሪያ ቤቶች ዉስጥ በከፍተኛ የኃላፊነት ቦታ ላይ ተመድበዉ የሚያገለግሉ ባለሙያዎች፣ ከፓርላማዉ ወንበር

ባልተናነሰ ሁኔታ እንደ ግዑዝ አካል የሚታዩ «የሕዝብ ተወካይ ነን» ባዮች በዚህ ምድብ ዉስጥ የሚገኙ ናቸዉ::

### 3/ በተቃዋሚነት ስም የሚንቀሳቀሱ አስመሳዮች

የመለስ ዜናዊ አምባገነን ስርዓት በኢትዮጵያና በሕዝቦችዋ ላይ ታሪክና ትዉልድ ይቅር የማይሉት ወንጀል በመፈፀም ላይ መሆኑን፣ የግዛት አንድነቷንና ሉዓላዊነቷን ለባዕዳን አሳልፎ በመሸጥ ላይ እንደሚገኝ በማጋለጥ በፅናት ቆመዉ የሚታገሉትን እዉነተኛ ተቃዋሚዎችና የኢትዮጵያ አንድነት ኃይሎች በዚህ ዉስጥ አይካተቱም::
እነሱ የሚወቀሱበት ጉዳይ ቢኖር በመካከላቸዉ በየወቅቱ የሚከሰቱ ልዩነቶችን አቻችለዉ በጋራ በመፍታት በቅድሚያ የጋራ ጠላት የሆነዉን ወያኔ ከማስወገድ ይልቅ በተቃራኒዉ ጥቃቅን ልዩነቶቻቸዉን በማጉላት በመካከላቸዉ አላስፈላጊ መከፋፈልን በመፍጠር የወያኔን ዕድሜ በማራዘማቸዉ እጅግ ልናዝንባቸዉ እንችላለን::

በዚህ በተቃዋሚነት ስም የሚንቀሳቀሱ አስመሳዮች በሚለዉ ስር የሚጠቀሱት ግን አንዳችም የረባ ለዉጥ ላያመጡ በተቃዋሚ ጎራ በመሰለፍ ነገር ግን ወያኔ የሚላቸዉን እየተቀበሉ በአገራችን የዲሞክራሲ ጭላንጭል ያለ ለማስመሰል በአጃቢነት ደፋ ቀና የሚሉትን ብቻ ነዉ:: እነዚህ ኃይሎች የወያኔን አምባገነን ገፅታ በዓለም አቀፉ ህብረተሰብ ፊት በመቀባባት ለእራሳቸዉ የሥራ ዕድል የፈጠሩ ለመሆናቸዉ አያጠያይቅም::

### 4/ የፍትህና የሚዲያዉ አካላት

ከፍተኛ ደረጃ የደረሰ የአዕምሮ መዛባት በሽተኛ እስካልሆነ ድረስ የአንድ ሰብዓዊ ፍጡር የሞራል ዕድገት ደረጃ መለኪያዉ ይነስም ይብዛ ለፍትህና ለሰብዓዊ መብት መርሆዎች የሚኖረዉ ግንዛቤ እንደሆነ የስነ ልቦና ጠበብት ይናገራሉ:: በዚህ ረገድ መርሆዎቹን ለመተርጎም፣ በሌላም በኩል ዜጎች በመርሆዎቹ ላይ እዉነቱን እንዲረዱት የማድረግ ኃላፊነት የተጣለባቸዉ አካሎች በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ከፍተኛ ኃላፊነት አለባቸዉ:: የፍትህ አካላቱ ማለትም ፖሊሱና ደህንነቱ፣ ወህኒና ፍርድ ቤቱ፣ የምርጫ አስፈፃሚ አካላቱ፣ በሚዲያዉ ዘርፍ የተሰማራዉ ክፍል በዚህ ዉስጥ የሚካተቱ ይሆናል:: እነዚህ አካላት ሙሉ በሙሉ በሽፍጥ ላይ ከተሰማሩ፣ ህሊናቸዉን የሸጡና የዘቀጡ ከሆነ አገርም ትዉልድም በየደረጃዉ እንደሚጠፉ በግልፅ መታወቅ አለበት::

ዛሬ በኢትዮጵያ ያለዉ ሁኔታ በዚህ ምድብ ዉስጥ የሚያገለግሉት ባለሙያዎች በቀጥታ ሕዝብ አደራ የሰጣቸዉ ወገኖች ባይሆኑም ከሌላዉ የሙያ ዘርፍ በተለየ መልኩ ለህሊናቸዉ እንዲገዙ የሚጠይቅ ፈታኝ ኃላፊነት እንደተጣለባቸዉ በቅድሚያ ጠንቅቀዉ ሊገነዘቡት የግድ ነዉ:: ከሕዝብ የሚያገናኝ፣ ባደባባይ የደረሱበትን ዉሳኔ የሚያሳዉቁበት፣ በዚህም የእራሳቸዉ ማንነትና ለእዉነት መቆም በይፋ የሚመዘንበት፣ በሌላም በኩል ዉሳኔያቸዉ በተቀባዩ ህልዉና ላይ በበጎም ይሁን በክፉ መልክ የሚያሳርፈዉ አሻራ በቀላሉ እንደማይፋቅ ሊረዱት ይገባል:: የፖለቲካ ሠራተኛ ካድሬ አድርገዉ እራሳቸዉን እስካልቆጠሩ ድረስ በሙያ ዕዉቀታቸዉ የሚያገለግሉ ከድኃዉ ግብር ከፋይ በሚገኝ ታክስ ደመወዝ የሚቆረጥላቸዉ ሲቪል የመንግስት ተቀጣሪ አድርገዉ እራሳቸዉን ከቆጠሩ በምንም መልኩ ቅድሚያ ሊሰጡና ሊያከብሩት የሚገባዉ ሙያቸዉን ነዉ፣ ከማንም በላይ:: እዚያ ወንበር ላይ ያስቀመጣቸዉ ጠመንጃ አንስተዉ የታገሉበት የፓለቲካ ትግላቸዉ ሳይሆን በትምህርትና ስልጠና የቀሰሙት የሙያ ተመክሯቸዉ መሆኑን ልብ ሊሉት ይገባል:: እራሳቸዉን ከአምባገነኖች ጥቃት በመጠበቅ አጋጣሚ በፈቀደ መጠን ከሕዝብ ጎን በመቆም የሙያ ተመክሯቸዉን ባግባቡ ካልተረጎሙ ህሊናቸዉ የሚጠይቃቸዉ መሆኑ ሊያስፈራቸዉና ሊያባንናቸዉ ይገባል::

በፈፀሙት ተግባር ሁሉ በያንዳንዷ ዕለት ሠላም አጥተዉ ዉስጣቸዉን ከሚያሰቃየዉ ሰቀቀን መጠነኛ እፎይታ ለማግኘት ፖለቲካዊ ግዳጅ ቢገጥማቸዉ እንኳ በተጓዳኝ ነፃ ሆነዉ የሙያ ግዳጃቸዉን የሚወጡበትን ቀዳዳ መፈለግ ይኖርባቸዋል፡፡
በተለይም የዳኝነት ስራ ለሙያ በእዉነት መቆም በምህላ የሚረጋገጥበት ነዉ፡፡ ዛሬ ላመነችበት ቃል በፅናት በመቆሟ ምክንያት አምባገነኑ የወያኔ ስርዓት ቃሊቲ እስር ቤት የሚያሰቃያት የአንድነት ለዲሞክራሲ ፓርቲ ሊቀ መንበር የሆነችዉ ወይዘሪት ብርቱኳን ሚደቅሳ ለሙያ ተግባሯ በነስዬ አብርሃ የወንጀል ክስ ችሎት ላይ ያሳየችዉ ዓይነት ቆራጥነት በሌሎች ዘንድ በየደረጃዉ እየተለመደ ቢሄድ ኖሮ በአሁኑ ወቅት የአገሪቱ ችሎቶች የቧልትና የፖለቲካ ተዉኔት መድረክ ባልሆኑ ነበር፡፡ አንዱ እዉነተኛ የሚወስደዉ ቆራጥ አቋም ለሌላዉ ትምህርት እየሆነ በመሄድ ብንማማር ኖሮ አደገኛ የሆነ የስነ ምግባር ዝቅጠት ዉስጥ እየወረድን አንሄድም ነበር፡፡ እነዚህ ኃይሎች ይዋል ይደር እንጂ በሕዝብ ድምፅ ወይንም በሕዝብ አመፅ ተሽቀንጥሮ ከሚወረወር ስርዓት ፖለቲከኞችና ካድሬዎች ጋር አብረዉ የሚወረወሩ ሳይሆን የተለዩ፣ የዳበረና የተከበረ ሙያ ያካበቱ፣ የሕዝብ አገልጋዮች አድርገዉ እራሳቸዉን ሊቆጥሩ ይገባል፡፡

አሁን በአገራችን የሚታየዉ ግን ከዚህ እዉነታ የራቀ ነዉ፡፡ የፍትህ አካላቱ ማለትም ፖሊሱና ደህንነቱ፣ ወህኒና ፍርድ ቤቱ፣ የምርጫ አስፈፃሚ አካላቱ፣ በሚዲያዉ ዘርፍ የተሰማሩት በሂደት ምንም ዓይነት የሞራል እሴት የሌለዉ፣ ዳኝነትና ፍትህን ተዓሚኒነት የሌለዉ የፈጠራ ስራ አድርጎ የሚመለከት ዜጋ የምናፈራበትን ጥርጊያ መንገድ በማዘጋጀት ላይ ባተኮረ አሳፋሪ ተግባር ላይ የተጠመዱ ይመስላል፡፡ ይህም እጅግ ዘግናኝ ተግባር እጅግ አሳሳቢ ነዉ፡፡ እነዚህ የህሊና ነፃነታቸዉን የሸጡ ዝቃጭ አካላት ለመጪዉ ትዉልድ በመተዉ ላይ ያሉት ታሪክ በምንም መመዘኛ አሳፋሪ ነዉ፡፡ በየመስኩ ለሃሰት ለሃሰት የሚቆም ትዉልድ እየኮተኮቱ እንደሆነ ሊገባቸዉ ይገባል፣ ይህም በቀጥታ አገርን ከመግደል ተለይቶ እንደማይታይ መታወቅ ይኖርበታል፡፡

## 5/ በዉጭ አገር የሚገኘዉ ለአገሩና ለአገር ቤት ወገኑ ደንታ የሌለዉ ኢትዮጵያዊ

አብዛኛዉ በዉጭ አገር የሚገኝ ኢትዮጵያዊ በተለይም ከግንቦት 97 ምርጫ ወዲህ የወያኔ አምባገነን ስርዓት በአገሩና በወገኑ ህልዉና ላይ በየወቅቱ የሚጭነዉ የግፍ ቀንበር፣ የሚያደርሰዉ ስቃይና እንግልት እንደእግር እሳት የሚያንገበግበዉ መሆኑ ከማንም የተሰወረ አይደለም፡፡ የስርዓቱን አምባገነንነት ለሚኖሩባቸዉ መንግስታትና ለዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት ተሟጋች ድርጅቶች ለማጋለጥ አስቸጋሪ በሆነዉ የአየር ጠባይ ሳይበገሩ መፈክር አንግበዉ፣ ጎዳና ወጥተዉ በረሃብ አድማና በሠላማዊ ሰልፍ ከመግለፃቸዉ በተጨማሪ ተቃዋሚ የፓለቲካ ድርጅቶች በመካከላቸዉ ያለዉን ልዩነት በዉይይት አስወግደዉ አንድነት በመፍጠር ቅድሚያ ተግባራቸዉ አምባገነኑን ስርዓት እንዲያስወግዱ በጊዜያቸዉ በጉልበታቸዉና በገንዘባቸዉ መስዋዕት በመክፈል ላይ እንዳሉ ገሃድ ማስረጃ ነዉ፡፡ በዚህ ያለመታከት የፈፀሙት ተግባር የመለስ ዜናዊ ማንነት በዓለም አቀፉ ህብረተሰብ ፊት ተቀባይነት እንዲያጣ አድርጎታል፡፡

ከላይ ከተገለፁት ባሻገር በዚህ በዉጭ አገር የሚገኘዉ ለአገሩና ለአገር ቤት ወገኑ ደንታ የሌለዉ ኢትዮጵያዊ በዚህ ምድብ ዉስጥ በተለያየ ደረጃ የምንመለከታቸዉ ናቸዉ፡፡
በመጀመሪያዉ ክፍል ዉስጥ የሚገኙት አገር ቤት መሬት በነፃ ለማግኘትና ጎጆ ለመቀለስ ከዚህ ካለፈም መጠነኛ የግል ድርጅት ለማንቀሳቀስ ካላቸዉ ፍላጎት በመነሳት በኢትዮጵያ በሚካሄደዉ የፖለቲካ እንቅስቃሴ ዉስጥ አንዳችም ምስልና ተሳትፎ እንዳይኖራቸዉ «አላይም፣ አልሰማም» በማለት እራሳቸዉን ሙሉ በሙሉ ያገለሉ የነገ ተስፈኞች ናቸዉ፡፡ እነዚህ ኃይሎች አገር ቤት ደጋግመዉ ደርሰዉ በመምጣት

ካዩዋቸዉ ሕንፃዎች፣ ዘመናዊ ተሽከርካሪዎች፣ ሆቴልና መደብሮች በመነሳት በኢትዮጵያ ዉስጥ ከፍተኛ የኢንቬስትሜንት ስራዎች በመከናወን ላይ እንደሚገኙና የሕዝባችን ሕይወት እየተለወጠ፣ ከፍተኛ የሆነ የኢኮኖሚ ዕድገት እየተመዘገበ መሆኑን የምጣኔ ሀብት ሊቅ ሆነዉ ምስክርነት ለመስጠት ሲንጠራሩ ይታያል።
በሁለተኛ ደረጃ የምናገኛቸዉ ደግሞ ከመስራትና በትርፍ ጊዜያቸዉ እራሳቸዉን ከማዝናናት ዉጭ በአገርና በወገን ላይ ምን እየተካሄደ እንዳለ በፍፁም የማይከታተሉ፣ ሙሉ በሙሉ ከመገናኛ ብዙኃን የተራራቁ፣ አልፎ ተርፎም አንዳንዶቹ በኢትዮጵያዊነት መታወቃቸዉን ለመደበቅ የሚዳዱ ሁሉ ይገኙባቸዋል።
በሶስተኛ ደረጃ ላይ የምናገኛቸዉ ደግሞ የዴሞክራሲ ባህል ባደገበት አገር ዉስጥ መኖራቸዉን በዉል ባለመረዳት በአገር ጉዳይ ላይ አፋቸዉን ሞልተዉ እዉነቱን ለመናገር ሲሸማቀቁ ይታያሉ።

ለማጠቃለል ያህል የወያኔ አምባገነን ስርዓት በያዘዉ ስዉር አጀንዳ መሰረት ኢትዮጵያ የምትባለዉን አገርና ሕዝብ በተገኘዉ አጋጣሚ ሁሉ ገዝግዞ ለመጣልና ለመግደል ሌት ተቀን ተግቶ በመስራት ላይ ይገኛል። የሕዝብን የምርጫ ዉሳኔ አክብሮ ስልጣን ለማስረከብ ምንም ፈቃደኛነት እንደሌለዉ፣ ይህንንም አምኖ ከተቀበለ በእግሩ በሚተካዉ የሕዝብ ይሁንታ በሚሰጠዉ መንግስት በእርግጠኝነት ሊወሰድ የሚችለዉ ህገ መንግስታዊ ማሻሻያ የመለስ/ስብሃት ቡድን ላለፉት 25 ዓመታት አሸምቀዉ ሲዘጋጁበት የነበረዉ የትግራይ ሪፑብሊክ ምስረታ እዉን እንዳይሆን እንቅፋት ይፈጥራል። ይህ እንዳይሆን በአምባገነንነት መቀጠሉን ብቸኛ ምርጫዉ አድርጎ ተቀብሎታል። ከወያኔ የለየለት ጠላትነት ባሻገር ዛሬ ለዚህች በየደረጃዉ ወደ ሚቆፈርላት መቃብር ለመዉረድ በሞት መንገድ በመጓዝ ላይ ለምትገኘዉ አገራችን ከላይ በየደረጃዉ በቁጥር የተጠቀሱት አካላት ከወያኔ ጎን በመቆም የዓላማዉ አስፈፃሚ በመሆን በሚፈፅሙት ተግባር ተጠያቂ ሊሆነየ እንደሚችሉ፣ ከሱ ባልተናነሰ መልኩ ከትዉልድና ከታሪክ ፍርድ እንደማያመልጡ በሚገባ ሊረዱት ይገባል። በሕዝባቸዉና በክልላቸዉ ኪሳራ ከወያኔ ለሚጣልላቸዉ የስልጣንና የጥቅም ፍርፋሪ ሲሉ አገርን በመግደል የወንጀል ተግባር ላይ መሳተፋቸዉንና ለባንዳ የተገዙ ባንዳዎች መሆናቸዉን ከእነሱ ባለፈ፣ቤተሰቦቻቸዉ፣ የቅርብ ዘመዶቻቸዉና «ሀይ ልንላቸዉ ይገባናል» የሚል እምነት ያላቸዉ ወዳጆቻቸዉ ሁሉ ሊገነዘቡት ይገባል።